# የጥሪው ካርድ ነውና "ከቆሸሸው ልብህ ወጥተህ በር ይዘህ ጠብቅ፤ በሩም ኢትዮጵያ ነዉ"።!!!

ኢትዮጵያ የግፉአን ምድር፤የጥቃት ሰለባ የሆኑ ሰዎችና ግፉአን ሞሉበት አገር ኢትዮጵያ !። ትብብር፣ መረዳዳትና መተሳሰብ የኢትዮጵያዊ ነታችን መልካም ገጽታ መግለጫ ጠፍቶ በሃገራችን እየሆነ ያለው ነገር በጣም የሚያስፈራ ነው ሃገራችን እንደ ሃገር ህልውና እንዳይኖራት፤ ኢትዮጵያዊው ሕዝብ አብሮ መኖር እንዳይችል አገሌ ከዚህ ክልል አገሌ ከዚህ ክልል ውጣ እየተባለ በሰው ዘር ላይ የሚፈጸም የመብት ጥሰትና የፍትሕ መጓደል ሌላውን ሰው ሊያሳስብና እንቅልፍ ሊነሳው ይገባል። በውጥረትና በቀውስ የተሞላ የዘር ቅራኔዎችን እያየን ነው የሚታየውና የሚሰማው ውስጥን ያደማል ከአገርነት ተርታ በሚያወጣ ቋፍ መገኘታችን በጣም ያስፈራል፡፡ የኢትዮጵያ መከራ የከፋ ሆኗል! የሚሰማ ቢገኝ! ዛሬ የኢትዮጵያ ጠላቶች ጠላቶቻችን ድምበር ጥሰው፣ ወታደር አሰልፈው፣ ጦር ሰብቀው አገር መውረር አያስፈልጋቸውም። እግራቸው ካገራቸው ሳይወጣ በዕጅ አዙር በለየላቸው ጨካኝ ወያ ኔ አገዛዝ ከእኛ ሊወስዱ የሚፈልጉትን መውሰድ ይችላሉ። እራሳችንን እንጠይቅ!? ዛሬ አንዱ ግፉእ አንዱ ተመልካች አንዱ ሯጭ የሚሆንበት የ ዝምታ ህመም ጊዜ አይሆንም።ይህ ደግሞ በትውልዱ በኢትዮጵያዊው በእኛ ትከሻ ላይ ያረፈ ችግር ነው ያገባናል! ላጥፊዎቹ አሳዳጆች መደበቂያ ጫካ ሆነን ኢትዮጵያዊያን እስከ መ ቸ መንገድ ላይ እንቅር? ብንጠላውም ታስረን እስከኖረን ድረስ መጠቃታችን አይቀርም።እስከ መቸ ታስረን እንኑር !!!??? ጆሮ ያለው ይስማ ኢትዮጵያ አደጋ ላይ ወድቋል ልንታደገው ይገባል!!!

ድርሻችንን እንወጣ እያንዳንዳች ወደ ራሳችን እንመልከት!!! እራሳችንን እንጠይቅ። " እስከመቼ "? በአገራችን በኢትዮጵያ እንደ ባይተዋር ፈርተን አንገታችንን ደፍተን የምንቀመጠው፣
በቁርጠኝነት እንነሳ ቁልፉ በእጃችን ነዉ። ለዉጥ ማምጣት እንችላለን የጥሪው ካርድ ነውና " ከቆሸሸው ልብህ ወጥተህ በር ይዘህ ጠብቅ፤ በሩም ኢትዮጵያ ነዉ"።!!! ኢትዮጵያን መጠበቅ ትችላለህ እስከ መጨረሻው።
በላይ ዘለቀ ሽህ ጦር አልነበረውም፤ እነራስ አረጋይ፤ቢትወደድ አዳነ፤ራስ አሞራው ውብነህም እንዲሁ። ራስህን ነፃ ለማውጣት ራስህ መንቀሳቀስ እንጅ አንተን ነፃ ለማውጣት ግዥ የሚፈጽም ወይም ጀግና የሚበደር ያለ አይመስለኝም።በጊዚያቸው ጀግነው ጀግንነትን የፈፀሙና ታሪክ ሠርተው ያለፉ አባቶቻችን እናቶቻችን እኛን ነፃ ሊያወጡ ከመቃብር ሊነሱ አይችሉም። ትንሾች መስዕዋትነት ከፍለው ሽዎችን ቢታደጉ ምንም ክፋት የለውም። "የዛሬን አብረኸኝ ቁም ከዚያ በኋላ እልሁ ያቆምሃል እንዳለችው "ጀምረው የሚጨርሰው ይመጣል።የጥሪው ካርድ ነውና " ከቆሸሸው ልብህ ወጥተህ በር ይዘህ ጠብቅ፤ በሩም ኢትዮጵያ ነዉ"።!!! እምነት ያሳርፋልና አምነህ ወጥተህ ጠብቅ፡፡ ኢትዮጵያን መጠበቅ ትችላለህ እስከ መጨረሻው።

***ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር !!!***

*ገብርኤል ብዙነህ*